مملكة البحرين
KINGDOM OF BAHRAIN

Public Awareness Campaign to Combat Coronavirus (COVID-19)

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች




healthalert.gov.bh

Amharic

## ክትባቱ እንዴት ይሰራል?

- ክትባት ሰዉነታችን ዉስጥ አንቲቦዲስ እንዲጨምርና፣ ከባክተሪያ እና ቫይረስ የመከላከል ሃይሉ እንዲጨምር ይረዳል።

## ለምን እከተባለሁ?

- ክትባት አንዱና ዋነኛዉ በሽታን የመከላከያ መንገድ ነዉ። ክትባት በሽታን ወደሌላ እንዳይተላለፍ እና በቫይረስ ምክንያት የሚመጣ ሞትን ይቀንሳል። የተመከሩ ክትባቶችን በጊዜዉ መዉሰድ በሽታን መከላለል እና አካባቢንም ከበሽታ ለመከላከል ይረዳል።

## ክትባት ይሰራል? ጉዳትስ የለዉም?

- በአጠቃላይ ክትባት ከጉዳት ጥቅማቸዉ ያመዝናል። ክትባት ጥቅም ላይ ከመዋላቸዉ በፊት አስፈላጊዉ ጊዜ ተወስዶ ምርምር እና ሙከራ ይደረግባቸዋል።

## ክትባቱ የተዘጋጀበት መንገድ አልፈጠነም?

- አልፈጠነም፣ ነገር ግን ያለዉን ሁኔታ ከግምት በማስገባት እና በጥር ወር ይፋ እንዲሆን በማለት በሚመለከታቸዉ ሳይንቲስቶቹ በፍጥነት እንዲሰሩ ፈቅዶላቸዋል። እንዲሁም ብዛት ያላቸው አገራት ፣ ሳይንሱ የሚፈቅደዉን መንገድ በመከተል ባህላዊ እና አዳዲስ መንገዶችን በመከተል ክትባቶቹን አዘጋጅቷል።

## የኮቪድ 19 ክትባት ከተወሰደ በኋላ ምን ጉዳት ያመጣል?

- ክትባቱ የተደረገበት ቦታ ትንሽ ህመም እና ማበጥ ሊያሳይ ይችላል። ምናልባትም ራስምታት፣ የማዞር እና ትንሽ ትኩሳት ሊያስከትል ይችላል።

## ምልክቶቹን ሲፈጠሩ ምን ማድረግ ይቻላል?

- እንደተሰማን ምልክት እና አመጣጣቸዉ ይወሰናል። ከላይ ለተጠቀሱት ህመሞች በቀላሉ ፔን ኪለር ሊወሰዱ ይችላሉ። ከበድ ያለ ህመም ካሎት ሃኪምን ማማከር ይመከራል።

## ክትባቱን ከመዉሰዴ በፊት ማወቅ ያለብኝ ነገሮች አሉ?

- ክትባቶን ከመዉሰዶ በፊት የኮቪድ 19 በሽታ ምልክቶች የሌሉበት ሊሆኑ ይገባል፣ ክትባቱ ለተሰራበት ኮምፖናንትም አለርጂይ ሊኖሮት አይገባም።

በክትባቱ ጊዜ ሴቶች እርጉዝ፣ ለእርግዝና የሚዘጋጁ እንዲሁም የሚያጠቡ ሊሆኑ አይገባም። የእርግዝና መከላከያ መወሰድ ያለበት ክትባቱ ከተወሰደ ከ 3 ወራት በኋላ መሆን አለበት።

## ክትባቱ የሚሰጠዉ በምን መንገድ ነዉ ፣ የቁጥሩስ መጠን?

- ክትባቱ በ21 ቀን ልዩነት ሁለት ጊዜ የእጅ ጡንቻ ላይ በመወጋት የሚሰጥ ይሆናል።

## ክትባቱን ለመዉሰድ የሚፈቀድለት ማን ነዉ?

- የኮቪድ 19 ክትባት ከ18 አመት በላይ የሆነ ሰዉ መዉሰድ ይችላል።

## በኮቪድ 19 ታመዉ የዳኑ ክትባቱን መዉሰድ ይችላሉ?

- ይችላሉ። ነገር ግን በኮቪድ 19 ተይዞ የነበረ ሰዉ፣ በበሽታዉ ከተጠቃ ከ90 ቀናት በኋላ መከተብ ይችላል።የጤና ሰራተኞች እና ተጋላጭ በታዎች ላይ የሚሰሩ ሰዎች የመከላከል ሃይላቸዉ ዝግጁ ባይሆንም መከተብ ይችላሉ።

## ክትባቱ ከተወሰደ በኋላ በኮቪድ 19 በሽታ መያዝ እንችላለን?

- እንደየሰዉ በሽታ የመከላከል አቅም ሊለያይ ይችላል። አንዳንድ ሰዎች በቂ በሽታን የመከላከል ሃይል ላይኖራቸዉ ይችላል፣
ክትባቱን ማግኘት ግን ከበድ ያሉ ምልክቶች እንዳይታዩ ያደርጋል።

## ለክትባቱ እንዴት መመዝገብ እንችላለን?

- የኮቪስ 19 ክትባትን ማግኘት ለምትፈልጉ ሚኒስቲር ኦፍ ሄልዝ ኦንላይን በመሄድ መመዝገብ ትችላላችሁ
Https://healthalert.gov.bh/